# እረ ዝም አትበሉ....!!

*የአቡን ወርቅ ጌታቸው (መምህርት)*

ምነዋ ገነነ አልቅጥ ተንዛዛ.....?
ለቅንጅት ችግር አናፋሹ በዛ፤
እንኳን ፖለቲካ - የሃሳብ ፍልሚያው አለም፤
የሃይማኖትም ዚቅ - ውዝግብ .... አያጣም፤
ታዲያ..! ለምን ይሆን? ገኖ መታየቱ ፤
የቅንጅት ጉዳይ የሃሳብ ልዩነቱ.....፤

ወገን ጎራ ጠርቶ - መዋቀስ ፣ መካሰስ ፣
ከጠረጴዛ አልፎ አደባባይ መድረስ፤
እገሌ አርበኛ - እገሌ ባንዳ ....ነው፤
ይሄኛው ሃቀኛ ያኛው ዳተኛ ...፤ነው
የምንባባለው.....?
ምክንያቱ ምንድነው...?

በነገር ሽብልቅ ስንጥቁን የማስፋት ፤
የብተና አዚም እርግማን ነው... ልክፍት ?

ቢሆንማ እንጂ! እርግማን ወይ ልክፍት፤
በደማችን ዘልቆ ጸበል የጠፋለት..፤
ከቶ ምን ሊባል ነው እንዲህ ያለ አደጋ ?
የረፋዱ ውህደት ማምሻው ላይ ሲናጋ !

እረ ደግም አይደል! ምንድነው? መራቆስ...፤
ጎዳና ያራሰው የሰው ደም ይታወስ.. !
የለጋው ወጣት በድን ጥይት የበሳሳው
እናቱ ብቻ ነች የምታስታውሰው...?
የነሽብሬ አካል ከምስጥ መዳበሉ.....፤
ለሕዝብ መብት እንጂ ከአፈር አይደል ውሉ!

እረ ዝም አትበሉ....!!

ዝም አይነቅዝም አይነት - ዝም ያላችሁትም!
ይሰማ ድምጻችሁ ዝምታችሁ ይቁም !
ያነቅዛል ዝምታ እራሱ ባይነቅዝም፤
ይሄንንም ወገን...አድብ እንበለው!
ያኛውንም ወገን ተበገስ እንበለው!
በጎራ ተጓርቶ ውዥንብሩን ይተው፤
በርግብግብ ምላሱ ጭሱን አያንድደው!
ዝም አይነቅዝም ብለን በዝምታ አንየው!
በቃህ እንበለው.....!

እረ ለመሆኑ ..? ወሬ አናፋሾቹ ፤
አንዱን አወድሰው አንዱን ዘርጣጮቹ፤
ነገ ሰላም ሲወርድ ስምምነት ሰፍኖ ...፤
እጅ ለእጅ ሲያያዝ ሁሉም አንድ ሆኖ፤
የነሱ ማረፊያ መድረሻ የት ይሆን?
ተወዳሽ ተኮናኝ ሁሉም አንድ ሲሆን፣
በምን ሊወራረድ..? የስም ማጥፋቱ እዳ፤
የምላሳቸው እድፍ በምንስ ሊጸዳ?

ይብላኝ ለነሱ እንጂ ... ለሽብልቆቹ፣
ሽንቁሩን ሰርጉደው ጎርፍ ጋባዦቹ፣
አጥንት ማዕዘኑ፣ የደም ሥጋው ምርጊት፤
ጣራና ግድግዳው፣ የቅንጅት ማጀት፤
እንኳን ምላስና ባሩድም ላይዘልቀው፤
በአጋዚ ጅብ መንጋ የተፈተነ ነው!!
ይብላኝ ለወሬኛው.....!!

ግራ ቀኝ አልልም ግራም ቀኝም የለም፤
ቅንጅት አንድ ነው ትናት ፣ዛሬም፣ ነገም፤

በወያኔ ዛቻ በእመቃው ሳይርዱ ፤
ለእጀ ሙቅ ለእግረ ሙቅ ሳይርበደበዱ፤
ለሕዝብ ኡ ባሉ ወህኒ የወረዱ..፤
ለኔም ላንተም ላንቺም የተሟገቱቱ፤
ትናት በሕዝብ ጩሀት ነጻ የወጡቱ፤
ኃይሉ፣ ብርሃኑ፣ ግዛቸው ፣ ብርትኳን ፤
በፈቃዱ ፤ያዕቆብ ፤ ፕሮፌሰር መስፍን፤
ብቻ ሁሉም.. ሁሉም...ጎራ ሳይለያቸው፣
ከአልማዝ የሚያበሩ የታሪክ ፈርጥ ናቸው፣
የቅንጅት መንፈስ ካህናቶች ናቸው ..
የሕዝብ ዋስ ጠበቃ....መመኪያዎች ናቸው!!

ታዲያስ ወገኖቼ ! እንዴት ዝም ይባላል?
ክብሩ እንደ ሙዝ ሲላጥ ለሕዝብ የቆመ አካል፤
እረ ዝም አትበሉ....

ዝም አይነቅዝም አይነት - ዝም ያላችሁትም!
ይሰማ ድምጻችሁ ዝምታችሁ ይቁም !
ያነቅዛል ዝምታ እራሱ ባይነቅዝም፤
ይሄንንም ወገን...አድብ እንበለው!
ያኛውንም ወገን ተበገስ እንበለው!
በጎራ ተጓርቶ ውዥንብሩን ይተው፤
በርግብግብ ምላሱ ጭሱን አያንድደው!

የቅንጅት መንፈስ ኃይልና ብርሃን፤
ይሰርጻል ይሰምራል አንድነት ስንሆን።